# የዘመን ቆጠራ ቅርሳችን

## ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ

ጌታቸው ኃይሌ

ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ) 1993 ዓ. ም.

==================================================================

"በዚህ መጽሐፍ ለማድረግ የሞከርኩት አበው (አባቶቻችን) ያቆዩልንን የባሕረ ሐሳብ ትምህርት በትውልዳችን ቋንቋ ማቅረብ ሲሆን ዓላማዬ ለማንም የአራት መደብ የተጥር ትምህርት ለተማረ ሰው (ከልሂቅ እስከ ደቂቅ) ባሕረ ሐሳብ የማውጣት ችሎታን ማስተማር ነው" (ገጽ 14)።

"የዛሬው ትውልድ ታሪክ ሲጠቅስ ብዙ ጊዜ ከአፄ ቴዎድሮስ ወደኋላ ሲሄድ ስለማልሰማ ከመጻሕፍቱ ጋራ በመስማማት ከሳቸው በፊት ያሉትን ዘመናት ለማስተዋወቅ ብዙ ገጾች ወስጃለሁ።:- አፄ ቴዎድሮስና ተከታዮቻቸው ነገሥታት ኢትዮጵያን ከወደቀችበት እናንሣ ሲሉ አገራችን ያሽበረቀችበትና የወደቀችበት ዘመን ነበረ ማለታቸው ነው" (ገጽ 229)።

"በምዕራፍ ፳ የተመዘገበው በዓውደ ሰማዕ(ታ)ት መጀመሪያ ጀምሮ በዓመተ ምሕረት (ዓ. ም.) እና በዓመተ እግዚእ (A. D.) መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳየው (ሠንጠረዥ) በኛ ዘመን ቆጠራዎች የተመዘገበን የታሪክ ድርጊት ወደ እነሱ የዘመን ቆጠራ (ወደ ዓመተ እግዚእ (A.D.)፥ በነሱ (በዓመት እግዚእ) የዘመን ቆጠራ የተመዘገበን የታሪክ ድርጊት ወደኛ (ወደ ዓመተ ምሕረት) የዘመን ቆጠራ ለማዞር የሚረዳ ነው"
(ገጽ 17)።

==================================================================

አለቺና "እውነት ነገር ብትናገር ትጸድቃለህ፤ ሐሰትን ብትናገር አንተ ትጠፋለህ" አለቺው:: "ተናገር ጥዩቀ እስመ ብእሲትከ ኢሞሖት" (እርግጡን ተናገር፤ ሚስትህ አልሞተችም) አለቺው፡: ያነግዜ ሰማና ነገርዋን እጅግ ደነገፁ: ምሽቱ እንደሆነቹቺ አላወቀም ነበረና:: ኋላ ግን ሲላት "እውነት ነው፥ እመቤቴ፤ በንጉሥ፥ በጳጳስበካህናት ፊት ሐሰትን እናገራለሁ፥ እግዚአብሔር ከገለጸልሽ ምግባሬን፥ ምሽቴቲሃአልሞተቺም" አለና ከጥንቱ እስከ ተፍጻሜቱ ነገራቸው:: ነጋዴ እንደነበረ፥ ከባልንጀራው እንደ ተባባለ (እንደተወራረደ)፥ እሌኒነም ከባሕር እንደ ሰደዳት ነገራቸው::
ያነግዜ እሌኒ ንግሥት ሰምታ "እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን፥ እውነት ነገር ያሰማኸኝ" አለቺና "በውነት አየኋት፥ ተናገርኋት፥ ከጸጐርዋ ነቅዬ አመጻሁ ብሎ ወርቅህን (ሀብትህን) ሰጠኸው?" አለቺው:: ""አዋን፥ እመቤቴ" አላት፡፡ ንግሥት እሌኒም፥ "ያ ነጋዴ በሕይወቱ አለን?" ብላ ጠየቀቺው፡: "አዋን፥ በሕይወት አለ" አላት:: "እስቲ ያነን ነጋዴ አምጹት" አለቺ። ጳጳሱም ያ ሰው ተጠርቶ እንዲመጻጻ አዘዘ። አመጹት። እሷም "ሞት በላይህ ያንዣብባል፣ እውነቱን ተናገር። የዚህን ነጋዴ ምሽት እውነት ወዳህ ወደሃት መጻህ?" ስትል ጠየቀቺው። ያ መልቲ ነጋዴም "ንግሥት እመቤቴ ' ሆይ፥ እግሬ ከዳጁም አልደረሰ፣ ዓይኔም ከእሷ ላይ አሳረፈ። በሌሎቹ ነጋዴዎቹ ፊት ተባብለን (ተወራርደን) ልወዳቅት፣ ልትወደኝ ብሄድ አልሆንልህ አለኝ። ቢቸግረኝ ገረዲቱን በወርቅ ደልዬ ደረቷ ላይ ካሉት ሶሶቱ ጸጐሯ አንዱን ነቅላ ዕንቁን ሰርቃ አመጣቺልኝ። ይኸነን ምልክት ይዤ ሄድሁ፤ በነጋዴዎቹ ፊት ያነን ፅንቅ ጸጐር አሳይቼ ረትቼ ባርያውነም፥ ማመሉነም፥ ወርቁነም፥ ብሩነም፥ ግምጃውነም፥ ሁሉነም ወሰድኩ -- ካንድ ልብስ በቀር" አለ።
ያነግዜ እሌኒ ንግሥት አመስግና "እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ሐሰቱን ያነጸርኅ (ያሳየህ)" አለቺ። ያነግዜ ያቺ ወስላታ ሴት በሕይወት አለቺን" ብላ ጠየቀቺ። ያ መልቲ ነጋዴ "አዋን በሕይወት አለቺ" አላት፡። እሌኒ ንግሥትም "ያቺን ሴት አምጿት" አለቺ። ወስላታዋ መጻች። ንግሥቲቱ ብትጠይቃት የሠራችውን ውስልትና ከጥንቱ እስከ ተፍጻሜቱ ተናዘዘቺ። "እርሱ መጻብኝ፤ አይቻለኝም አልሁት። ወርቅ ቢያሳየኝ፥ ወደ እሌኒ ገብቼ "ባልሽም መጻ፥ ገላሺን የሚያጽብሽ ሰው የለ አልሁና ገላዋን ሳጽባት ከደረቷ ከሶስቱ ጸጐር ሐንዱን ነቀልሁና ከዕንዮሩ ጨምሬ ሰጠሁት። እርሱም ወርቁን ሰጠኝና ሄደ። የውነት ነው" አለቺና ተናገረቺ።፡

ከዝያ ኋላ እሌኒ ንግሥትም "በተሀብሎ (በውሸት) ነገር ወስደህ ከባሕር ጣልኸኝ። ቤትኸን አጠፋህ፣ ንዋየ ወርቅኸን ሁሉ ሰጠኸው በሰሚዓ ነገረ ኂጣን" (የአታላዮች ነገር በመስማት) አለቺና "እኔ ግን እግዚአብሔር በነፍሴ ይፍረድ፣ ከእግዚአብሔር ነገር ሌላ ምንም አላውቅ። ሠራሽ ይከተልሽ ብለህ ከባሕር እንደጣልኸኝ ይኸው ሥራዬ ተከትሎኝ የበረንጥያ ንጉሥ አገባኝ። ከእሱም ክርስቶስን የሚወድ ልጅ ወለድኩ። መስቀሉነም ፈልጌ አገኘሁ፤ አሁን እንግዲህ ቤተ ክርስቲያናትና ገዳማት አሠራለሁ" አለቺና (እንዲህ የሚል) ፍርድን አስፈረደቺ፡

(ገጽ - 63)
*__በነገረ ዓመፃ እንጂ አሌኒነስ ያስገደላቿኋት። የነጋዴ ተርቢኖስን ወርቁን ሁሉ መልስ፣ መላስህ፥ ቀኝ ክንድህ ይቴረጽ፡ ወስላታዋ ሴት ትኩኖ አመተ (ባርያው ትሁን)__*
አሰኝታ፥ ወርቁን ሁሉ ለባሏ አስመልሳ፧ ከዝያ ኋላ ሀገረ ኢየሩሳሌም ሄደቺ፡ ልትሄድ ስትል ጳጳሱ ሲሸኛት "መስቀሉን በምን ወራት አገኘሽው" ብሎ ጠየቃት:: "በመጋቢት በ፲ ቀን አገኘሁት" አለችው:: እሱም እንግዴህሰስ (ይህ ዕለት) በዓል ይሁን አለና ዓዋጅ ነገረ።

ኢትዮጵያውያን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት አባቶቻችን ይኸንን ዛሬ የሚሠሩበትን የዘመን ቁጠራ ዘዴ (ባሕረ ሐዓዝን) ያገኙት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን መሆኑን ጠቁሜያለሁ: ኢትዮጵያ በሃይማኖት በኩል ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ያላትን የግንፔነት ታሪክ የሚያውቅ በዚህ አይገረምም። ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተደረሱትን የግዕዝ የሃይማኖት መጻሕፍት ከውጪ አገር (በተለይም ከመካከለኛው ምሥራቅ) ወደኢትዮጵያ ያመጣናቸው በአብዛኛው ከግብፅና በመጠኑ ከሶርያ ቤተ ክርስቲያን አግኝተናቸው ነው::
ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት፥ ሕዝቦች ሁሉ ዘመንን ለመለካትና ለመቀ-ጠር ሞክረዋል፦ እኛ ዛሬ የያዝነውን የዘመን አቄጣጠር ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ብናገኘውና ከራሳችን ቁጠራ ጋራ ብናስተባብረውም፡ የፋርስ፥ የሮማ፥ የአይሁድ፧፣ የዐረብ ሊቃውንት ተመራምረው የደረሱበት ውጤት (ፍሬ) ነው።

## ዘመን ቁጠራ ለቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ዘመን ቂቁጠራ ያስፈለጋት በዓላትና አጽዋማት በየዓመቱ የሚውሉበትን ቀን ለማወቅ ነው፧: ሁለት ዓይነት በዓላት አሉን:: ዓይነታቸውን ሁለት ያደረጉብን የትንሣኤ ጉዳይ ነው:: አንድን በዓል ዓመቱን ጠብቆ በዓመቱ በዚያው ዕለት ማክበር የተለመደ ነው:: ለምሳሌ፥ ቅዱስ ሚካኤል የሚከበረው ኅዳር 12 ቀን ነው:: ባመት ባመቱ ኅዳር 12 ሲመጣ የሚካኤል ቀን ብለን እናከብረዋለን: ኅዳር 12 ቀን ከሳምንቱ ዕለቶች በየትኛውም (ሰኞ፥ ማክሰኞ፥ ወዘተ.) ሊውል ይችላል። በሆነው ዕለት ቢውል ግድ የለንም፥ ያንን ዕለት የሚካኤል በዓል አድርገን እናከብረዋለን:: ትንሣኤን ግን በዚያው ክርስቶስ ከሞት በተነሣበት በእሑድ ቀን እንዲሆን ፈለጉ:: እንዲህ ከሆነ በየዓመቱ በዓሉ የሚውልበት ወር በገባ በተወሰነ ቀን፡ ለምሳሌ፣ በዚ።ው ከሞት በተነሣበት ዕለት በመጋቢት 29 ቀን ልናደርገው አንችልም። ጥንተ ትንሣኤ እሑድ መጋቢት 29 ቢሆንም መጋቢት 39 ቀን ሁል ጊዜ እሑድ ቀን አይውልልንም፤ ከሳምንቱ ቀኖች በሣንኛውም- ዕለት ሊውል ይችላል፧ ስለዚህ ክርስቶስ ከሞት የተነሣበት ዕለት እሑድ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ በያመቱ በእሑድ ዕለት ሊያደርጉት ወሰኑ:: ይኸ እንዴት ሊሆን ይችላል? ሁለት ፈልጎ (መጋቢት 29 ንም እሑድንም) አይሆንም:: - ቀኑስ እሑድ መሆኑን በምን ዐወቁት?

(ገጽ 64)
ክርስቶስ ከሞት የተነሣው እሑድ ዕለት መሆኑስ አያጠራጥርም፡: አንደኛ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያኖች በአፍ ታሪክ ያቆዩልን ቀን ነው:: ሁለተኛም÷ ምሁራኑ ሐዲሰ ኪዳንን ሲመረምሩ ክርስቶስ የተሰቀለው ዓርብ ዕለት፣÷ ከሞት የተነሣጦ ዓርብን ጨምሮ ከሶስት ቀን በኋላ በመጣው እሑድ ዕለት መሆኑን ተረድተውታል። እንዴት?

እንዴት ማለት መልካም ነው:: ፍሥሕ የአይሁድ በዓል እንደሆነ እናውቃለን:: እኛ ክርስቲያኖች ትንሣኤን "ፋሲካ" የምንለው የአይሁድ ፍሥሕ ለክርስቶስ ሕማማትና ትንሣኤ ትንቢት ስለነበረ ነው:: ጌታና ደቀ መዛሙርቱም (ተማሪዎቹ) አይሁዶች ስለነበሩ እንደማንኛው ይሁዲ በዓሉን እንዳከበሩ አንብበናል (ለምሳሌ ሣቴ. ም. 26):: ይኸ የሆነው ጌታን ለፍርድ ለማቅረብ በያዙበት ሳምንት ውስጥ ነው:: ዕለቱ ኀሙስ ነበረ ለማለት ይቻላል:: ያን ዕለቱን ማታ ወታደሮች መጥተው ጌታን ሲአልይ አግኝተው ያዙት (በዚህም ዕለቱ ጸሉተ ኀሙስ ይባላል):÷ በማግሥቱ ከሀገረ ገገርው ከጲላጦስ ልንጤናዊው ላይ ክስ መሥርተው ስቅላት አስፈረዱበት፤ ወዲያው ሰቀሉት:: በቅዳሜ ቀን ምንም ሥራ ስለማይሠሩ ሬሳውን ያን ዕለታውኑ (በሰንበት ዋዜማ) ከሰዓት በኋላ ከመስቀል አውርደው ቀበሩት (ማር. ም. 15 ጐጥር 42 እስከ 547)፡-- እንደ ሀገሩ ልማድ ሴቶች ዘመዶቹ በሳልስቱ እሑድ ሰለት ("በሰንበትም መጨረሻ በመጀመሪያው ቀን") ወደመቃብሩ ቢሄዱ መቃብሩን ባዶውን አገኙት (ማቴ. ም. 28)። "በሰንበት መጨረሻ" ማለት ተርጓሚ ሳያስተካክለው ቀርቶ ነው እንጂ "በሳምንቱ መጨረሻ" ማለት ነው:: ሳምንቱ የሚጨረሰው ከቅዳሜ በኋላ ነው፡ኔ: ከዚያ ቀጥሉ "በመጀመሪያው ቀን" ይላል:: "መጀመሪያ ቀን" ማለት "እሑድ" ማለት መሆኑን ቀደም ብለን ተናግረናል:: ግዕዙማ በቀጥታ ""ወበእሑድ ሰንበት" ነው የሚለው::

በ 217 ዓ.ም. ኒቅያ ላይ የተሰበሰቡት 318 አበው ቅዱሳን ጳጳሳት ካሳለፏቸው ውሳኔዎች አንዱ ትንሣኤ ሁል ጊዜ እሑድ ቀን እንዲውል ነው:: ይኸንን ለማድረግ ዓመቱን ጠብቆ ለዚያ (ለመጋቢት 29) በቀረበው እሑድ ማዋል በጣም በቀለለ ነበረ። እነሱ ግን ትንቢቱን ሁልጊዜ ሕያው ለማድረግ ሲሉ ከአይሁድ ፍሥሕ ጋራ ያለው ግንኙነት ቋሚ እንዲሆን በማሰብ፣ የአይሁድ ፍሥሕ ከዋለበት ቀን በኋላ የሚመጣውን እሑድ የትንሣኤ መታሰቢያ እንዲሆን ወሰኑ:: ትንሣኤ ዓመቱን ጠብቆ በዚያው ቀን መሆኑ ከቀረ ትንሣኤን ተከትለው የሚመጡ በዓላትና አጽዋማ ሁሉ (ለምሳሌ፤ ስቅለት፣ ጳራቅሊጦስ፣ ወዘተ.) ከትንሣኤ ጋራ ሲንፏቀቁ ሊኖሩ ነው:፡

ይኸ ውሳኔ ለክርስቲያኖች ዘላለማዊ ችግር ፈጥሮባቸዋል፤ ምክንያቱም አይሁድ (ፍሥሕን ጨምሮ) በዓሎቻቸውን የሚያከብሩት ዘመንን በጨረቃ እየቆጠሩ ነወ። በዚህ ምክንያት የአይሁድ ፍሥሕ በፀሐይ አንደሚቆጠረው በዓመት ውስጥ በተወሰነ ቀን አይውልም።- አሁን አንግዴህ የአይሁድ ፍሥሕ የሚውልበትን ቀን በየዓመቱ እየፈለግን ትንሣኤን ከፍሥሕ ጋራ አዛምደን ማክበር ግድ ሆነ።

የአይሁድ ፍሥሕ እሑድ ቀን ቢውልስ? "ይኸ ጥሩ አጋጣሚ ይሆናል" የምንል እንገኝ ይሆናል። የኒቅያ ጉባኤ አበው ግን አንደዚህ አላዩትም:: አይሁድ ክርስቶስ) ስላልተቀበሉ፡ አንዲያውም እሱን አስሰቀለው አሱን የተቀበሉትን ክርስቲያኖችንም ስላሰቃዩ፣ በተለይም ቅዱስ አእሰጢፋኖስን (የመጀመሪያውን ሊቀ ዲያቀን) በድንጋይ

(ገጽ 65)
ወግረው ስለገደሉት፣ እነሱ ዓ፦ሐቸውን ሲያከብሩ ክርስቲያኖች ትንሣኤን ከነሱ ጋር በዚያን ጊዜ አብረው እንዳያከብሩ ከለከሉ፤ አብሮ መደሰት ይመስልብናለ አሉ።

**በዘመን አቈጣጠር ከምዕራብ ክርስቲያኖች ለምን ተለየን?**

ክብ የሆነ ነገር ሲለካ ከየትኛውም ቦታ ሊጀመር ይቻላል ብለናል።: ዓውደ ዓመትም ይኸው ነው:: ዋናው ነገር አንድ ታላቅ ታሪካዊ ድርጊት ፈልጎ እሱን መነሻ ማድረግ ነው: ለምሳሌ፣ ሮማውያን የሮም ከተማ የተቈረቈቈረችበትን ዘመን መነሻ አድርገውት ነበረ። ታላቁ እስክንድር የገነነበትም የዘመን መጠሪያ ሆኖ ነበር። የኛ ካህናትም "ዘመነ እስክንድር" በሚል ስም ይጠቀሙበት እንደነበረ የብራና መጻሕፍታችን ይመሰክራሉ። ሶርያውያን የሮማውያንን የዘመን አቈቈጣጠር (ማለት በፀሐይ ቈጥሮ ለዓመቱ 365/6 ዕለት መስጠትን) ከሮማውያን በተዋሱ ጊዜ የዓመቱን መጀመሪያ ("ርእሰ ዓውደ ዓመት" ይባላል) ጥቅምት (ኦክቶበር) ] ቀን ላይ አድርገውት ነበረ:: በኋላ የሰማዕ(ታ)ት መታሰቢያ እንዲሆን በ 460 ዓ. እ. ወደ መስከረም (ሴፐቴምበር)፣ ቀን ለወጡት። ግብፆችና እኛ ርእሰ ዓውደ ዓመታችንን በመስከረም፣ ቀን ያደረግነው ይኸንን በመከተል ሳይሆን አይቀርም:: የመጀመሪያው ጳጳሳችን ፍሬምናጦስ የሶርያ ሰው ነበረ።:-. ከሱ በኋላም ብዙ የሶርያ መነኩሳት ኢትዮጵያ መጥተው መንፈሳዊ አባቶቻችን ሆነዋል:: የዓመቱን መጀመሪያ በመስከረም ማድረግን ከሶርያውያንም ሆነ ከግብፆች ብናገኘውም ጀማሪው በ 46 ቅ. ክ. ሮምን ይገዛ የነበረው ቄሳር ዩልዮስ ስለነበረ የዩልዮስ ባሕረ ሐሳብ፤ (Julian Calendar ) ይባላል።

እንደእውነቱ ከሆነ ዓውደ ዓመትን (የአንድን ዓመት ዘመን) ምን ጊዜም ቢደመር በወርና በቀን መክፈል አይቻልም፣ በዘፈቀደ ካልሄድን በቀር ከ 365 ዕለት ውጪ ያሉትን <u>5 ሰዓት፥ ከ 48 ደቂቃ፥ ከ 46 ዳግሚት</u> (ሰከንድ) ምን እናድርጋቸው? ቄሳር ዩልዮስ በ 46 ቅ. ክ. (ቅድመ ክርስቶስ) ባወጣው የዘመን አቈጣጠር ሥርዓት መሠረት ዓመቱን 365 ዕለት <u>ከ 5 ሰዓት</u> አድርጎ ለአራቱ ወሮች 30 30 ዕለት ለአንዱ 28/29 ዕለት ለቀሩት ሰባት ወሮች 3! 3! ዕለት መድበላቸው !2 ቦታ ከፈለው፣ 12 ወሮች መሆናቸው ነው:: እኛ በዓመቱ ቀኖች ተስማምተን ቀኖቹን በወር ስንከፍል ,ችለይተናል፡ኔ: ዋናው ነገር ኝመቱ ውስጥ ባሉት ሰለቶች መስማማታችን ነው::

የቄሳር ዩልዮስ አከፋፈል አድልዎ ያለበት ይመስላል፤ አንዳንድ ወሮች 31 ቀን ሲሰጣቸው አንዳንዶቹ ፤() ብቻ ተሰጥቷቸዋል፥፤ ያለምክንያት አይደለም:: ዋናው ጥያቄ ግን ይህ ነው:- ዓመቱን 365 ዕለት፥<u> ከ 5 ሰዓት፣፥ ከ 48 ደቂቃ፥ ከ 46 ዳግሚት (ሰከንድ) </u>በማድረግ ፈንታ፥ 1! ደቂቃ፣ ከ 14 ዳግሚት (ሰከንድ) ከየት አምጥቶ ነው 365 ዕለት፥ ከ 6 ሰዓት (365 ከ 1/4) ያደረገው ይኸን አከፋፈል (ይኸንን የሌለ ጊዜን ጨምሮ መቀጠር) በ 1582 ዓ. እ. የነበሩ (የኢየሱሳውያን) ሊቃውንት ሲመረምሩት ሁለት ስሕተቶች አስከትሉ አገኙት:፦ አንደኛ ቂሳሩ አከፋፈሉ እንዲመቸው ሲል የጨመራቸው ትርፍ ደቂቃዎችና ዳግሚቶች ኢምንት ቢሆኑም በዘመን ብዛት ተጠራቅመው የሌለን 10 ቀን አምጥተዋል:: ሁለተኛ የጸደይን እኩሌ በዚያው ልክ (110 ቀን) አናግተው በመጋቢት 25 ቀን (March 21) በማረፍ ፈንታ ቀደም ብሎ

(ገጽ - 66)
መጋቢት 15 ቀን (እ/8 ርከ 1!) ላይ እንዲያርፍ አድርገውት ነበር፡ነ: በ 1582 ዓ. እ.
የሮም ፖፕ የነበረው ግሬጎሪ (13 ተኛው ጎርጎርዮስ) በስሕተት የተከማቹትን 10 ቀኖች ቆርጦ ጣላቸው: በዚያን ዘመን (በ 1575 ዓ. ም.) ጥቅምት 1 ቀን የዋለው በ 28 September (1582 ዓ. እ) ነበረ፥ በዚያ አካሄድ ጥቅምት 8 በ October 5 ቀን እንዲሆን ሲጠበቅ ጳጳሱ ያንን ዕለት October 15 ቀን አደረገው:: ሰው ሁሉ ″ዛሬ October 5 ቀን (ጥቅምት 8) ነው″ ሲል፥ እሱ “የለም ዛሬ October 15 ቀን (ጥቅምት 18) ነው″ ብሉ 0 ወጀ:: ከ October 6 ቀን (ጥቅምት 9) አንሥቶ እስከ October 14 ቀን (ጥቅምት 17) ያሉትን ቀኖች መቸ ኖርንባቸውና ነው ዛሬ October 15 ቀን (ጥቅምት 18) ነው የምትለው?” ቢሉት “በየዓመቱ ላይ የሌለንን ደቂቃና ዳግሚት እየጨመርን ኖረንባቸዋል″ አላቸው ይባላል:: እኛ ኢትዮጵያውያን ዓዋጁን አልተቀበልነውም፤ በዚያው ከቄሳር ዩልዮስ ባገኘነው ጸንተናል:: የኢትዮጵያና በምዕራባውያን አቈጣጠር ወሮቹ እኩል በአንድ ቀን የማይጀምሩት (በአሁኑ ጊዜ 10 ቀን፥ ዘመኑ ሠርግ ሲሆን በ 11 ቀን፥ የሚለያዩት) በዚህ ምክንያት ነው::

አሁንም ቢሆን እኮ የዓመቱ ጊዜ ከሩጾ ደቂቃዎች እና ከ 46 ዳግሚቶች (ሰከንዶች) በፍራክሽንም (በክታፊም) ቢሆን ትንሽ ይበልጣል:: በየ 4 ዓመቱ አንዱ ዓመት 366 ዕለት እንዲኖረው የተደረገው 24 ሰዓት የማይሞላውን ዘመን ሞልቷል በማለት ነው: አራተኛውን ዓመት አንድ ዕለት ያስጨመረለት ዘመን (ጊዜ) 22 ሰዓት፥ ከ 15 ደቂቃ፥ ከ 4 ዳግሚት ብቻ ነው:: ይኸ (24 ሰዓት ስላይደለ) አንድ ዕለት አይደለም፡ጹ: ያንን አንድ ዕለት (24 ሰዓት) ለማድረግ በዘፈቀደ 45 ደቂቃ ከ 56 ዳግሚት ተጨምረዋል። እነዚህ ተጠራቅመው በየ 00 ዓመት 2 ዕለት ይወጣቸዋል፡:ሱ፥ ስለዚህ ምዕራባውያን በየ 400 ዓመቱ አንድ ዕለት ሠግር (leap year) እያደረጉ ሦስቱን ግን መጣል ይኖርባቸዋል፤፥ ለዚህም ዓመቱን 365 ከ 97/400 በማድረግ ተዘጋጅተዋል። በኛና በነሱ መካከል ያለው ልዩነት በዚያው ልክ እየሰፋ ሄዶ በ 1582 ዓ. እ. በመስከረም ወር የነበረው የ 8 ቀን ልዩነት ዛሬ በዚያው በመስከረም ወር 11 ደርሷል፡: እርማቱን ካልተቀበልን ልዩነቱ እየሰፋ ይሄዳል፡፡ የከዋክብትን ሂደት የሚያጠኑ ሊቃውንት (የአስትሮኖሚ ሳይንቲስቶች) የሐሳቡን ትክክልነት (ማለት፥ የዩልዮስ ባሕረ ሐሳዝብ መለወጥ እንዳለበት) ተቀብለውታል።

እዚህ ላይ፣ ሌላ መጠቀስ የሚገባው ባሕረ ሐሳብ አለ:: በ 1079 ዓ. እ. ቡመር ኸያም የተባለው የታወቀው የፋርስ (ኢራን) ባለቅኔና የከዋክብት ሊቅ፣ የጸደይ እኩሌ ዓውድ የሚፈጀው ጊዜ 365 ከጾ/32 ቀን እንደሆነ አሳይቶ ነበር። ይህም ክፍለ ጊዜ (period) ከጎርጎርዮሱም (365 ከ 97/400) ሆነ ከዩልዮሱ (365 ከ 1/4) ክፍለ ጊዜ ይልቅ የጸደይ እኩሌን ትክክለኛ ቦታ ይጡብቃል፡: ፖፕ ጎርጎርዮስም፥፣ ከመረጠው ክፍለ ጊዜ ይልቅ የዑመር ኸያም የ 33 ዓመት ዓውድ መሻሉን ያውቅ ነበር።

በዚህ የ 33 ዓመት ዓውድ መጠቀም ዘዴው ቀላል ነው። መጀመሪያ ዓመተ ምሕረቱን በ 33 እንገድፈዋለን። ተረፉ (ትርፉ) ከ 0 (ዜሮ) እስከ 32 ይሆናል። ተረፉ 0 ከሆነ፥ ዓመቱ አይሠግርም፡ ተረፉ ከ 0 ከበለጠ ግን ተረፉን እንደገና በ፥ እንገድፈዋለን። አዲሱ ተረፍ 0 ከሆነ፥ ዓመቱ ይሠግራል።፡

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን አቆጣጠር በከፊል ከዩልዮስ ቄሳር ዘመን አቈጣጠር የተዛመደ እንደሆነ አመልክቻለሁ። በከፊል ደግሞ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ዘመን አቈቈጣጠር በተለየም ከዘመነ ሰማዕ(ታ)ት ጋራ የተያያዘ መሆኑንም አይተናል። ዓመቱንም ሁላችንም እንደምናውቀው 30 ዕለት ያለባቸው 12 ወሮችና የቀሩትን 5/6 ዕለቶች 13 ተኛ ጦር ቋግሜ (ጳጉሜን) አድርገን ከፍለነዋል። አማርኛ ተናጋሪዎች "ጳጐሜን" በማለት ፈንታ "ቋግሜ" የሚሉት የ"ጳ" ድምፅ በአማርኛ ስለአልነበረ ነው። ("ጰ" በአማርኛ አለመኖሩን ያወቅነው "ጳ" ያለበት የአማርኛ ቃል ስለሌለ ነው። "ጴጥሮስ"÷ "ጳውሎስ" "ጳራቅሊጦስ"÷ "ጳንጠቆስጤ"፣ ""ጳጳስ"÷ "ጠረጴዛ" በመሠረቱ አማርኛ አይደሉም

እኛ ኢትዮጵያውያንም ሆንን ምዕራባውያን ዘመናችንን የምንቈጥረውና <u>ዓመተ ምሕረት</u> (ዓ. ም.)÷ <u>ዓመተ እግዚእ</u> (ዓ. እ.) የምንለው ከክርስቶስ ልደት ጀምረን ከሆነ ለምንድነው ክርስቶስ የተወለደበትን ቀን የወራችንና የዓመታችን መጀመሪያ ያላደረግነው? ምዕራባውያን ክርስቶስ በዲሴምበር 25 ተወለደ ይሉና ዓመታቸውን ከአንድ ሳምንት የበለጠ ጊዜ ካለፈ በኋላ በጃንዋሪ ይጀምራሉ፡ እኛ በታኅሣሥ 29 ቀን ተወለደ እያልን ዓመታችንን የምንጀምረው ወደኋላ ሄዴን በመስከረም ነው:: ይኸ አልበቃ ብሎ እኛና ምዕራባውያን ክርስቶስ የተወለደበትን ዘመን ስንቈጥር በ?ገ/8 . ዓመት እንለያያለን። እኛ የክርስቶስን እድሜ ደብቀን ወጣት ልናደርገው 7/8 ዓመት ቀንሰንለት ነው ወይስ ከልጅነቱ ጀምሮ ያስተምር በነበረበት ጊዜ ውሎው ከአይሁድ ሊቃውንት (ከረበናትና ከጸሐፍት) ጋራ ስለነበረ እንደነሱ ሽማግሌ ለማድረግ ምዕራባውያን 7/8 ዓመት ጨምረውለት ነው?

መጀመሪያ የመጀመሪያውን ጥያቄ ለመመለስ ልሞክር፣ ክርስቶስ ታኅሣሥ በገባ በ 29 ወይም በዲሴምበር 25 ተወለደ ማለት ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት ዘመን ቈጠራ እንደ ነበረ ያሳያል፤ በዚያን .ጊዜ የኛ ወር ታኅሣሥ የነሱ ወር ዲሴምበር ነበረ፡ ክርስቲያኖች የክርስቶስን መወለድ ለዘመን ቈጠራ መነሻ ሲያደርጉት እስከዚያ የነበረውን ዘመን (የዓመት ተጥር ብዛት) ጣሉት እንጂ የልደቱን ቀን ርእሰ ዓውደ ዓመት (የዘመን መለወጫ) አላደረጉትም:: የዘመን መለወጫውን ጊዜና የወሮቹን ስምና አካሄድ ሳይለውጡ በዚያው ቀጥለዋል፡፡-- ስለዚህ በኛ አገማመት ክርስቶስ የተወለደው ታኅሣሥ 29 ቀን፣፡ 1] ዓ. ም. (ወይም ታኅሣሥ 329 ቀን 5501 ዓ. ዓ.) ነው። ከመስከረም 1 ቀን እስከታኅሣሥ 29 ቀን 1 ዓ. ም. ያለው ዘመን (ከመስከረም 1 ቀን 5501 እስከ ታኅሣሥ 29 ቀን 5501 ዓ. ዓ. ያለው ዘመን) "ዓመተ ምሕረት" የተባለው ክርስቶስ የተወለደበት ዓመት ስለሆነ ብቻ ነው:: አባባሉን ልንነቅፈው አይገባም፤ አንድን ድርጊት በእንደዚህ ያለ ዓመተ ምሕረት ተፈጸመ ስንል (ለምሳሌ÷ ይና ና በ 1888 ዓ. ም. ተፈጸመ ስንል) ድርጊቱ በዚያ ዘመን <u>ውስጥ</u> ተፈጸመ ማለታችን እንጂ በዚያ ዓመተ ምሕረት መጀመሪያ ላይ ተፈጸመ ማለታችን ኣይደለም::

እኛ ክርስቶስ በታኅሣሥ 29 ቀን 1 ዓ. ም. ተወለደ ስንል እነሱ በዲሴምበር 25 ቀን 1 ቅድመ ክርስቶስ (ቅ.ክ.) ተወለደ አሉ:: ልዩነቱ እየሰፋ መጥቶ፣ ባሁኑ ዘመን በ 13 ዕለት የተለያየነው ከላይ እንደገለጥሁት ፓፕ ግሪጎሪ ያስተካከለውን (ያረመውን)

የቄሳር ዩልዮስን ዘመን አቈጣጠር ስላልተቀበልነው ነው::

አሁን ደግሞ ወደሁለተኛው ጥያቄ ልሂድ፤ ክርስቶስ የተወለደበትን ዓመት አስመልክቶ እኛና ምዕራባውያን በ 7/8 ዓመት የተለያየነው ክርስቶስን ወጣት ጦይም ሸማግሌ ለማድረግ ሳይሆን ካለማወቅ በመጣ ስሕተት ምክንያት ነው:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ቅድስት ማርያምን “ወለተ ነዳያን” (የድኾች ልጅ) እንደሚሏት፣ ክርስቶስ የተወለደው ካንድ ደኻ ቤተ ሰብ ከመሆኑ ሌላ ዘመኑ ልጆች በቤታቸው ሲወለዱ ፅለቱ በየቤቱ በመዝገብ በማይያዝበት ዘመን ነው:: በኛም አገር ቢሆን በቤተ መንግሥት፥ በመኳንንትና በምሁራን ቤት ካልሆነ በቀር ልጅ የተወለደበትን ዕለት መዝግቦ መያዝ የተለመደው የምዕራባውያን ትምህርት በቀመሰው ትውልድ ቤት ነው፡:- በሕዝብ ዘንድ ግን “አድዋ በተዘመተ በዓመቱ ዐረፈ/ች”፥ “የሰገሌ ዘመቻ በሆነ በሶስት ዓመቱ ተወለደ/ች”፥ ወዘተ. ነው የሚባለው:: አገር ቤትማ ገበሬው "ልጅህ እድሜው ስንት ነው?” ሲሉት መልሱ ልጁ በፈጀው ደበሉ ተቈቁጥሮ ″3 ደበሉሎ″"፣ “4 ደበሉ ጨርሷል″ ይሆናል፡ አንዱን ደበሎ አስረጅቶ ለመጣል ምን ያህል ጊዜ ይፈጅበታል? የክርስቶስ ቤተ ሰብ (ቅዱስ ዮሴፍና ቅድስት ማርያም) ክርስቶስ የተወለደበትን ቀን መዝግበውትም እንደሆነ መዝገቡ አልተገኘም።

በትንቢቱ መሠረት አይሁድ የክርስቶስን መምጣት ይጠባበቁ እንደነበረ ስለሚታወቅ እውተኛው ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ብዙ ሰዎች “እኔ የምትጠብቁት ክርስቶስ ነኝ″ በማለት አጭበርብረዋል፡-፡ እውነተኛው ክርስቶስ ሲመጣ እሱም እንደሌሎቹ አንድ የሚያጭበረብር ሰው መስሏቸው ነበረ፤ የሰቀሉትም በዚህ ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል (ለምሳሌ፥ ማቴ. ም. 27፥ ቍ.. 39-44)።- ኢየሱስ እውነተኛው ክርስቶስ መሆኑን ለመቀበል የዓለም ሥልጣናት ከሶስት መቶ ዓመት የበለጠ ጊዜ ፈጅቶባቸዋል፡ በዚያን ጊዜ ወደኋላ ሄደው “ለመሆኑ ክርስቶስ የተወለደው መቸ ነበረ?” ብለው ታሪክ መመርመር ጀመሩ፡-- ግን ብዙ ማስረጃ አላገኙም፤ ስለሱ የሚናገር መዝገብ አልተገኘም:: እርግጥ ሄሮድስ የሚባል ንጉሥ ይሁዳን ይገዛ በነበረበት ጊዜ፥ በሰማይ ላይ ትልቅ ኮከብ በታየበት ጊዜ (ሰብአ ሰገልን የመራቸው)፥ የሮማው ቄሳር አውግስጦስ "እኔ የምገዛው ሕዝብ ሁሉ ይቈጠር″ ብሉ ትእዛዝ በሰጠበት ዓመት መወለዱን፥ በአይሁድ ላይ የተሾመው ሮማዊ ገዢ የጳንጤኑ (ጳንጤናዊው) ጴላጦስ በነበረበት ጊዜ መሞቱን (መሰቀሉን) ወንጌሎቹ ይመሰክራሉ ። ግን ታሪኩን መርምረው ዘመኑን ለነገሩን አበው ሊቃውንት በጃቸው የነበረው መረጃና ምናልባትም የነሱም ችሎታ በቂ ስላልነበረ የተወለደበትን ዘመን ሲቀምሩ ተሳስተዋል። አሁን በኋላ የተነ ሊቃውንት ምንጮቹን በመመርመር ከዘመኑ ላይ ምዕራባውያን 7 ዓመት እኛ 15 ዓመት እንደቀነስንለት ይናገራሉ፤ እንዲህ ከሆነ የተወለደው በኛ 15 ዓመት፥ በነሱ 7 ዓመት ጨምረን ዛሬ 1992 ዓ. ም. ወይም 2000 ዓ. እ. መሆኑ ቀርቶ (1992 + 15 ወይም፥ 2000 + 7 =) 200” ዓ. ም,ዓ. እ. ነው። የሁለተኛው ሺህ ዓመተ እግዚእ መጀመሪያ ነው ብለን ዘንድሮ ያከበርነው ፅለት ባለፋ በሰባት ዓመቱ ነው ።

# ምዕራፍ ፪

## የባሕረ ሐሳብ አወጣጥ

ጳኮሚዮስ ልታልቅና አዲስ ዓመት ሊጀምር ሲል ተንቀሳቃሽ በዓላትና አጽዋማት በሚቀጥለው (በአዲሱ) ዓመት ምን ምን ቀን እንደሚሆኑ ሕዝበ ክርስቲያኑ ለማወቅ ስለሚፈልግ መምህሩ ባሕረ ሐሳ 4ብ ያወጦጣል፡ "ባሕረ ሐዓዝብ ያወጣል" ማለት ከአበው (ከአባቶቻችን) በተማረው መንገድ፥ "ዓለም ተፈጠረበት፥ ዘመን ቁጠራ ተጀመረበት" ከሚባለው ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ 5500 ዓመት ጀምሮ ሒሳቡን አስቦ፥ ዕለቶቹን ቀምሮ በዓላቱ ምን ምን ቀን እንደሚውሉ፥ አጽዋማቱ ምን ምን ቀን እንደሚጀምሩ ይናገራል ማለት ነው:: በምዕራፍ ስ፡ (ገጽ 45 እና 63 "ዓውደ ቀመር" እና "ዘመን ቁጠራ ለቤተ ክርስቲያን" በሚሉ ንኡስ አርእስት ስር) ለምሳሌ ያህል እንዳመለከትነው ተንቀሳቃሽ በዓላት የሚባሉት የነነዌ ጾም፥ ዓቢይ ጾም (ሁዳዴ)፥ ደብረ ዘይት፥ ሆሣዕና፥ ስቅለት፥ ትንሣኤ፥ ረክበ ካህናት፣ ዕርገት፥ ጳራቅሊጦስ (ጳንጠቆስጤ)፥ ጾመ ሐዋርያት (የሰኔ ጾም)፥ ጾመ ድኅነት ናቸው። እነዚህ በዓላትና አጽዋማት (ሌሎችም እዚህ የማንተቻቸው በዓላት) በአንድነት ሲታዩ 532 ዓመት ሙሉ በየዓመቱ በተለያዩ ቀኖች ይውላሉ:: ምክንያቱንም እንደተናገርነው በጨረቃ የዘመን አቁጣጠር (በዓውደ አበቅቴ) ላይ ስለተመሠረቱ ነው።: መምህሩ ቁጠራውን ዓለም ከተፈጠረበት (ከ 5500 ቅድመ ክርስቶስ) የሚጀምረው ያለነው ከያዝነው ዓውደ ቀመር በየትኛው ዘመን (በተለየም በየትኛው ዓውደ አበቅቴ) እንደሆነ ለማወቅና የዚያ ዘመን በዓላትና አጽዋማት የሚውሉበትን ዕለቶች ለማውጣት ነው:: 28 የተለያዩ ዓውደ አበቅቴዎች ኣሉ፤ እኛ ያለንበት ዓውደ ለበቅቴ አ 2«ቱ ያትኛው እንደሆነ ካላወቅን ያበዓ 4 ቱንና የኣጽዋማቱን ቀን ለማወቅ ለንቻልም:: ለመምህሩ ለቅመራው ታላቅ ርዳታ የሚሆንለት በተሰጠው ዓውደ አበቅቴ ውስጥ እንደምንም አስቦ ከነዚህ በዓላትና አጽዋማት አንዱ የሚውልበትን (በተለየ የነነዌ ጾም የሚጀምርበትን) ዕለት ካወቀ፣ ዕውቀቱ ለሁሉም በቂ መሆኑ ነው:: እነዚህ በዓላትና አጽዋማት እርስ በርሳቸው በተወሰኑ ቀኖች ስለሚራራቁ እነሱ የሚውሉበትን ቀን ለማግኘት ባንዱ በተገኘው በዓል ላይ እነዚያን የተወሰኑትን (የሚራራቁበትን) ቀኖች መደመር ነው:: ለምሳሌ፥ ስቅለት ምን ቀን እንደሚውል ካወትን በዚያ ላይ ሁለት ቀን በመደመር ትንሣኤ የሚውልበትን ቀን ልናውቅ እንችላለን። ሌሉቹ በዓላት ሁሉም ከነነዌ በኋላ ስለሚመጡ መምህሩ መነሻ የሚያደርገው የነነዌ ጾም የሚገባበትን ቀን ነው። እነዚያ መራራቂያ ቀኖች ነነዌ በባጀችበት (በገባችበት) ዕለት ላይ ተደማሪዎች ስለሚሀት በባሕረ ሐሳብ ቋንቋ ተውሳክ ይባላሉ። ተውሳክ ማለት "ተጨማሪ" ማለት እንደሆነ ከቡር ብላታ መርስዔ ሐዘን ወልደ ቂርቆስ "ተውሳከ ግሥ" ሲሉ በአማርኛ ሰዋስዋቸው አስረድተውናል:: የነነዊ ጾም የሚጀምርበትን ቀን ጐጥር ደግሞ "ባጀ" (ቆየ፥ ባለበት ረጋ) ከሚለው ግሥ ተነሥተው መቆያ ለማለት መባኛ ሐመር ይሉታል:: "ሐመር"